ጽሑፍ እና ሥዕል፡- ዊልያም ዴ ቪንክ

# መሲሑ ኢየሱስ

የምንጊዜም ታላቁ ታሪክ።



# ዋና ዋና ቃላት. .



**ኃጢአት** - እኛ የምንፈጽመው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይስማማና እርሱ ወዳኖረልን ግብ እንዳንደርስ የሚያግደን ነገር (ገጽ 4)

**መልአክ** - የማይታይ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ገጽ 5)



**መመለስ** - ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ ማንኛውም ነገር አዲስ ይሆናል። እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ያድሳል (ገጽ 57)።

**መሲሕ** - ‹‹የተቀባ ንጉሥ›› መሲሕ የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፣ በግሪክ ክርስቶስ ተብሎ ተተርጉሞአል። (ገጽ 52፣ 55)።



**መስቀል** - በገዛ ራሱ ፈቃድ ኢየሱስ የሞተበት የማሰቃያ መሣሪያ፤ ከኢየሱስ ሞት ወዲህ መስቀል የተከታዮቹ ሁሉ ምልክት ሆኗል (ገጽ 25, 50)።

**መንፈስ ቅዱስ** - የኢየሱስ ተከታዮች በሆኑ ሰዎች ውስጥ የሚኖር የእግዚአብሔር መንፈስ (ገጽ 58)።



**መጽሐፍ ቅዱስ** - እግዚአብሔር ሰዎችን ስለሚያይበትና ከእነርሱም ጋር ስለሚያደርገው ግንኙነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ይቻላል።

**ሰይጣን** - የማይታይ የእግዚአብሔርና የሰዎች ጠላት፤ ዲያብሎስ ተብሎም ይጠራል።



**በረከት** - እርሱ የሚፈልገውን ለሚያደርጉ ሰዎች እግዚአብሔር የሚሰጠው መልካም ነገር ሁሉ።



**ትንሣኤ** - ኢየሱስ ከሞት መነሣቱ፤ አንድ ቀን ደግሞ ሰዎች ሁሉ ከሞት ይነሣሉ፤ ከዚያም እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሰው ይፈርዳል (ገጽ 53-57)።

**ኢየሱስ** - የእግዚአብሔር ልጅ ስም ሲሆን፣ ‹‹እግዚአብሔር ያድናል›› ማለት ነው።

**እምነት** - እግዚአብሔር የተናገረው ቃል እንደሚፈጸም አምኖ መቀበል።

**የእግዚአብሔር ልጅ** - ይህ የኢየሱስ ስም ነው። እርሱ ሰው በመሆን ወደዚህ ምድር የመጣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

**የእግዚአብሔር መንግሥት** - ሰዎች ለእርሱ በሚታዘዙበት ቦታ በዚያ የእግዚአብሔር መንግሥት ይኖራል።

**የዘላለም ሕይወት** እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት ከኢየሱስ ጋር የምንኖረው ሕይወት። ሞትን ያሸንፋል፤ ማለቂያም የለውም (ገጽ 23፣ 29-30 እና 59)

**የጌታ ራት** - በእንጀራውና በወይኑ አማካይነት የኢየሱስ ተከታዮች የእርሱን ሞትና ትንሣኤ የሚያስታውሱበት

**ይቅርታ** - ምንም እንኳ የሚገባን ባይሆንም፣ እግዚአብሔር ይቅር ይለናል፤ በኃጢአታችን ከተጸጸትንና ከዚያ ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆንን እግዚአብሔር ይቅር ይለናል። ኢየሱስ እኛ የሚገባንን ቅጣት ስለ ተቀበለ ይቅር መባል እንችላለን (ገጽ 58)።

**ደቀ መዝሙር** - የኢየሱስ ተከታይ (ገጽ 18)

**ጸሎት** - ጸጥ ብለን ወይም ድምፃችንን በማሰማት ለእግዚአብሔር መናገርና ከእርሱም መስማት (ገጽ 18፣ 19፣ 42)።

**ፋሲካ** - የኢየሱስ ትንሣኤ የሚከበርበት በዓል። አይሁድም ፋሲካን የሚያከብሩት በዚሁ ቀን ነበር።



## መሲሕ ኢየሱስ ማን ነው?

ከ2,000 ዓመት በፊት ኢየሱስ በእስራኤል ይኖር ነበር። ‹መሲሕ ኢየሱስ› ወይም፣ ‹ኢየሱስ ክርስቶስ› በማለት እንጠራዋለን። እርሱ ንጉሥ ቢሆንም፣ ንጉሥ ብቻ አልነበረም። ኢየሱስ፣ ‘የእግዚአብሔር ልጅ’ ተብሎም ይጠራል፤ ከዚያም በላይ እርሱ፣ ‹‹የሰው ልጅም›› ነው። ይህም ማለት እርሱ እግዚአብሔርም ሰውም ነው ማለት ነው። የኢየሱስ ሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል። ይህ የዘመናት ሁሉ ትልቁ ታሪክ ነው።

## ኢየሱስ የመጣበት ዘመን

ዘመናችን የሚጀምረው ከኢየሱስ መወለድ ነው። በዚያ ዘመን ሰዎች የሚጓጓዙት በእግር ወይም በአህያ፣ በግመል ወይም በፈረስ ነበር። አብዛኛው የአውሮፓ፣ የመካከለኛው ምሥራቅና የሰሜን አፍሪካ ክፍል በሮም መንግሥት ተይዞ ነበር። አብዛኛው ሕዝብ ማንበብ መጻፍ አይችልም ነበር፤ ማንበብ መጻፍ የሚችሉት በእስራኤል ምድር የነበሩ አይሁድ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች፣ ‘የመጽሐፉ ሰዎች’ ይባሉ ነበር።

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ በሚባለው መጽሐፍ በኩል ይናገራል። እርሱ ሕልውና ያላቸው ነገሮች ሁሉ ፈጣሪ ሲሆን፣ የሰዎች ሁሉ ወዳጅ መሆን ይፈልጋል። ኢየሱስ ይህን በግልጽ አሳይቷል!






# እስራኤል በኢየሱስ ዘመን

ዋና ከተማ ኢየሩሳሌም

**አውራጃዎች**: ገሊላ፣ ሰማርያ፣ ይሁዳ

**ስፋት**: በግምት 28,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ወይም 10,810 ስኩዌር ማይሎች

**የአየር ሁኔታ**: ከፊል ሐሩራዊ

**የፖለቲካ ሁኔታ**፣ ከኢየሱስ መወለድ በፊት ከነበረው ጊዜ ማለት በ63 ከክ.በ. (ከክርስቶስ ል በፊት) ጀምሮ እስራኤል በሮማውያን ቁጥጥር ሥር ነበረች።

**በዘመኑ** የነበሩ ገዦች ሮማዊው ባለ ሥልጣን ጴንጤናዊው ጲላጦስ እስራኤል ይገዛ ነበር፤ የእርሱ አለቃ ሮማዊው ንጉሥ ጢባሪዮስ ነበር።

**ሃይማኖት** ይሁዲነት። አይሁድ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ነበራቸው። ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ሥራ የሚያከናውኑ ካህናት ነበሩ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ሕዝቡን የሚያስተምሩ ፈሪሳውያን የመሳሰሉ አስተማሪዎች ነበሩ።

**ቋንቋዎች** የአይሁድ ቋንቋ ዕብራይስጥ ሲሆን፣ ግሪክ የዚያ አካባቢ ሕዝብ ሁሉ ቋንቋ ነበር፤ ላቲን የሮማውያን ቋንቋ ነበር።


እነዚህ ኹሉ ሰዎች ወንዙ ዳር የተሰበሰቡት ለምንድን ነው?
የእግዚአብሔር መንግሥት መጥታለች፤ ራሳችሁን አዘጋጁ!


ዐዲስ ሕይወት ጀምሩ!
ከእግዚአብሔር አታመልጡም የፍርዱ መጥረቢያ በዛፎች ሥር ተቀምጧል...
መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ኹሉ ተቈርጦ ወደ እሳት ይጣላል!
እኛ ኹላችንም ተቈርጠን ልንጣል ነው?፤ ሕይወታችን መልካም አይደለምን?
አዎን! ማንም ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይችልም። ነገር ግን ከእኔ በኋላ ኹለንተናችሁን መለወጥ የሚችል ይመጣል።
በእውነት ሕይወታችሁ እንዲለወጥ ከፈለጋችሁ፤ ኀጢአተኞች መኾናችሁን እመኑ፤ ከዚያ ወደዚህ ውሃ መጥታችኹ ተጠመቁ!
አሁን ከኀጢአታችሁ ነጽታችኋል፤ ስለዚህ ዐዲስ ሕይወት መኖር ጀምሩ!



በወንዙ ዳር ኾኖ ይሰብክ የነበረውን ሰባኪ ሰዎች መጥምቁ ዮሐንስ ይሉት ነበር...
እኔ ይህን ያህል አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ አይደለሁም፤ እኔ የእግዚአብሔርን ማንነት ለሚያሳየን ለርሱ መንገድ እያዘጋጀኹ ነው። ርሱ በእግዚአብሔር መንፈስና በእግዚአብሔር እሳት ያጠምቃችኃል። ያኔ ኹለንተናችሁ ይለወጣል!
ከዚያም...
... ይልቁን እኔ በአንተ መጠመቅ አለብኝ!
ግዴለም አንተ አጥምቀኝ፤ እንዲህ በማድረግ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንፈጽማለን።
አባት ኾይ፣ መንግሥትህ ትምጣ፤ የአንተ ፈቃድ ይፈጸም!
ከሰማይ እንዲህ የሚል ድምፅ መጣ...
አዎን፣ አንተ የምወድኽ ልጄ ነኽ፤ በአንተም ደስ ይለኛል።



መጥምቁ ዮሐንስ ለሚመጣው መሲሕ እስራኤልን እያዘጋጀ የነበረው የዛሬ ኹለት ሺሕ ዓመታት ነበር፤ በዚያ ዘመን እስራኤል በጣም ሰፊ በነበረው የሮም መንግሥት ውስጥ በጣም ትንሽ ቦታ የያዘች አገር ነበረች።
እስራኤል
ቅፍርናሆም
ናዝሬት
ቃና
ገሊላ
ዮርዳኖስ
ኢየሩሳሌም
ይሁዳ
በእስራኤል የነበሩ አይሁድ ጭቆና ውስጥ ነበሩ፤ ከዚያ ለመላቀቅ ዐቅም አልነበራቸውም። ሕዝቡም መሲሑ የሚመጣበትን ጊዜ ይጠባበቁ ነበር። ርሱ በጥንታውያን የአይሁድ መጻሕፍት ውስጥ እንደሚመጣ ትንቢት የተነገረለት አዳኝ ነው። ይህ መሲሕ የእግዚአብሔር ፍትሕ አሸንፎ እንዲወጣ ያደርጋል።
በዮርዳኖስ ወንዝ የነበረው መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ በማመልከት...
ተመልከቱ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚብሔር በግ ይኸውና አለ።
ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ምድረ በዳ መራው።
ርሱም በዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየ፤ በዚያ ቆይታውም ምንም አልበላም። የሚጠብቀው ሥራ ምን እንደ ነበር በግልጽ ለማየት ሲጸልይና ሲጾም ነበር።
ኢየሱስ ዓለምን በሞትና በጥፋት ይገዛ የነበረው የማይታየው ጨለማ ገዢ ሰይጣንን ተቃወመ።
በዚያ ሁኔታ ሲያልፍ ኢየሱስ በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ግልጽ ማድረግ ነበረበት። የእግዚአብሔር ዕቅድ ሰዎች ከሞት ፍርድ ነጻ እንዲወጡ ማድረግ ነው።
አዎን፤ አባት ኾይ፤ አንተ የምትፈልገ ውን አደርጋለሁ!


ነገር ግን ተቃዋሚው ሰይጣን የእግዚአብሔርን ተልእኮ ከመፈጸም ሊያዘናጋው ወደ ኢየሱስ አሳሳች ሐሳቦችን ለማምጣት ሞከረ።
በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንኽ እስቲ እነዚህን ድንጋዮች ዳቦ አድርጋቸው!
በፍጹም አላደርገውም! ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር መጽሐፉ ውስጥ ተጽፏል።
አንተ በርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ ከኾንኽ በተግባር አሳይ! ከቤተ መቅደሱ ጣራ ወደ መሬት ዝለል። የእግዚአብሔር መላእክት እንደሚያነሡኽ ተጽፎአል አይደል?
እግዚአብሔርን አትፈታተን ተብሎም ተጽፏል።
አንተ ወድቀህ ብትሰግድልኝ፤ በምድር ያለውን ሥልጣንና ኀይል ኹሉ እሰጥሃለኹ!
አንተ ሰይጣን ከእኔ ራቅ! እኛ ማምለክና ማገልገል ያለብን እግዚአብሔርን ብቻ እንደ ኾነ ተጽፏል።
ከዚያም ሰይጣን ከኢየሱስ ተለይቶ ኼደ፤ መላእክትም መጥተው አገለገሉት...
ኢየሱስ ወደ ገሊላ የተመለሰው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር። ኢየሱስ ያደገው ብዙ ሕዝብ ይኖር በነበረበት ሰሜናዊ የእስራኤል አውራጃ ነበር። እየተጓዘ እያለ ብዙዎች ዐብረውት ኾኑ። ኢየሱስ ነቢያት ትንቢት የጻፉለት መሲሕ መኾን አለመኾኑን ለማየት ጓጉተው ነበር።


በኮረብታማው የገሊላ አካባቢ ባለው ቃና በሚባል ቦታ ሰርግ ነበር...
ኢየሱስና እናቱ ከጥቂት ወዳጆቹ ጋራ ወደ ሰርጉ ቦታ ተጠርተው ነበር።


ግን ግብዣው እየተደረገ መሐል ላይ...
ችግር ተፈጠረ! ወይን ጠጁ አለቀባቸው!
ኢየሱስ የሚነግራችኹን አድርጉ!
ትልልቅ እንስሮቹን ውሃ ሙሏቸውና የግብዣው አሳላፊ እንዲቀምስ ስጡት።
?
ውሃ አልነበረም እንዴ? አሁን ግን ወይን ጠጅ ኾኗል! ለዚያውም ምርጥ ወይን ጠጅ!
ቅመሰው! ምርጡን ወይን ጠጅ እስከ አሁን ድረስ አቆይተኻል!
እንዲህ ያለ ነገር ሰምቼ አላውቅም! ይህን በሚመስል ሰርግ ተገኝቼ አላውቅም፤ ወደ ምርጥ ወይን ጠጅ የተለወጠ ውሃ ጠጥቼ አላውቅም!
ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሥራ ነው?
ለመሆኑ፣ ርሱ ማን ነው?


ቅፍርናሆም ገሊላ ባሕር አጠገብ የምትገኝ ሀብታም የዓሣ ማጥመጃ ሰፈር ናት። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በተመለከተ በአደባባይ መናገር የጀመረው እዚህ ነበር!
የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት የመረጠውም ከዚህ ስፍራ ነበር።
ጴጥሮስ፣ ወደ ጥልቁ ባሕር እንቅዘፍና መረብኽን ጣል።
ጌታ ኾይ፣ ሌሊቱን ሙሉ ስንደክም ብናድርም ምንም አልያዝንም።
አንተ ካልኸ ግን...
በፍጹም ማመን አልችልም።


ያዕቆብ! ዮሐንስ! ወደዚህ ኑ፤ ለዕድሜ ልካችን የሚበቃ ዓሣ አጥምደናል!
ጌታ ኾይ፣ እኔ በጣም ኀጢአተኛ ነኝ፣ ከእኔ ተለይ።
ጴጥሮስ፣ አትፍራ!
ይልቅ መጥተኽ ተከተለኝ፤ ሰዎችን የምታጠምድ አደርግኻለሁ!
ተከተለኝ!
9


ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለሰው ኹሉ እየተናገረ፣ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በመላው ገሊላ ተመላለሰ። ማንኛውንም ዐይነት ደዌ ፈወሰ፤ አጋንንታዊ መናፍስትን አስወጣ፤ ሰዎቹም በጣም ተደንቀው ተከተሉት፤ ከሌሎች አካባቢዎችና የእስራኤል ዋና ከተማ ከኾነችው ከኢየሩሳሌም እንኳ ሳይቀር ሰዎች ወደርሱ ይመጡ ነበር። ርሱ የሚናገረውንም ኹሉ ሰሙ...
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ስለ ኾነች ድኾች የተባረኩ ናቸው።
ጽድቅን የሚራቡ የተባረኩ ናቸው፤ ይጠግባሉና።
የሚያለቅሱ የተባረኩ ናቸው፤ እንደ ገና ይሥቃሉና።
በእኔ ምክንያት ሰዎች ሲነቅፏችሁ የተባረካችሁ ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ስለኾነ ደስ ይበላችሁ ሐሤትም አድርጉ።



ሌሎች ሰዎች እንዲያደርጉላችኹ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው።
ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ ደግሞም ጸልዩላቸው።
መልካም ነገር ስታደርጉ የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ብላችሁ አታድርጉ፤ በስውር አድርጉ።
ከርሷ ጋራ ለመተኛት በመጓጓት ወደ ሴት የሚመለከት፤ በልቡ ከርሷ ጋራ አመንዝሮአል።
ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ዐይንህ ጤነኛ ከኾነ መላው አካልኽ ብሩኅ ይኾናል። ዐይንህ በጭጋግ ከተጋረደ ግን በጨለማ ትኖራለህ።
ማንም ለኹለት ጌቶች መገዛት አይችልም፤ እግዚአብሔርንና ገንዘብን ማገልገል አይቻልም።
ስለ ነገ አትጨነቁ።በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስቀድሙ፤ ሌላው ነገር ኹሉ ተከትሎ ይመጣል።
ቃሎቼን ብትከተሉ ቤቱን በዐለት ላይ እንደ ሠራ ሰው ትኾናላችሁ፤ ቃሎቼን የማትከተሉ ከኾነ ግን ቤቱን አሸዋ ላይ እንደ ሠራ ሰው ትኾናላችሁ።



አንድ ቀን ሰዎች ቅፍርናሆም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቤት መጥተው ነበር...
በፍጹም መግባት አንችልም።
አዎን ጣራው ላይ ነው፤ ምንጣፍና ሌላ ነገርም ይታያል!
እዚያ ላይ ምን እየኾነ ነው?
ተዋቸው! እነዚህ ሰዎች ትልቅ እምነት አላቸው!
ኀጢአትኽ ይቅር ተብሎልኻል!
የተናገረውን ሰማችኹ? እንዴት እንዲህ ይላል?
እግዚአብሔርን እየተሳደበ እኮ ነው!
የሰውን ኃጢአት ይቅር ማለት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው!
ለመኾኑ ለዚህ በሽተኛ፤ ኀጢአትኽ ይቅር ተብሎልሃል ከማለትና ተነሣና በእግርህ ቁም ከማለት የቱ ይቀልላል?
መሲሑ ኀጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን አለው፤ እኔ ግን ጨምሬ፤ ምንጣፍህን ይዘህ ተነሣና ተመላለስ! እላለኹ።


በጣም ይገርማል!
አዎን፣ መራመድ ችያለሁ!
ሰውየው እየተራመደ ነው!
ግን ኢየሱስ ባደረገው ነገር ደስ ያላቸው ኹሉም አልነበሩም። የሃይማኖት መሪዎቹ ኢየሱስ የሰንበትን ሥርዓት ያከብር እንደ ኾነ እየጠበቁ ነበር። በእስራኤል በዚህ ቀን ማንኛውንም ዐይነት ሥራ መሥራት በጥብቅ የተከለከለ ነበር።
ይህ ሰው እጁ የሰለለ ነው፤ ታዲያ፣ በዚህ ቀን መፈወስ ተፈቅዷልን?
እጅህን ዘርጋው!
ተመስገን፣ ተፈውሻለኹ!
ይህ ሰው ሕዝቡን እያሳተ እንደ ኾነ ኢየሩሳሌም ላሉት መሪዎች መነገር አለበት።
ይህን ሰውዬ ማጥፋት አለብን!
13.


ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋራ በገሊላ ባሕር በጀልባ እየኼደ ነበር።
ጌታ ኾይ፣ ድረስልን! እየሰጠምን ነው!
ለምን ፈራችሁ? እምነታችሁ የታል?


ጸጥ፣ ረጭ በል!
ጀልባቸውን ባሕሩ ዳር አሰሩ፤ ተራራው ላይ ግን...
የጩኸት ድምፅ


ተራራው ላይ አንድ አጋንንት ያደሩበት ሰው ነበር።
ርሱ እየመጣ ነው!
አዎን፣ እየመጣ ነው!
አዎን፣ አዎን፣ ኢየሱስ ራሱ ነው!
እናንተ ርኩሳን መናፍስት ልቀቁት!
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ኾይ፣ ከአንተ ጋራ ምን ጉዳይ አለኝ?
ስምህ ማን ነው?
ብዙ ስለሆንን ስሜ ሌጌዎን ይባላል።
ወደ እነዚያ ዐሣማዎች እንድንገባ ፍቀድልን።
ኺዱ!


?
ሙሉ በሙሉ ድኛለኹ!
ኺድ! እኛን ተወን!
ከአንተ ጋራ ልምጣ?
አይሆንም እዚሁ ኹን። እግዚአብሔር ያደረገልህን ለሰዎች ኹሉ ተናገር!


ወልድ በራሱ ምንም ማድረግ እንደማይችል እነግራችኋለሁ። ርሱ የሚያደርገው አብ ሲያደርግ ያየውን ብቻ ነው። የአባቴን ፈቃድ እንጂ፣ የራሴን ፈቃድ አላደርግም። እኔን የላከኝም ርሱ ነው።
ኢየሱስ ለጸሎት ሁሌም ወደ ጸጥተኛ ቦታ ይኼድ ነበር።
ሌሊቱን በጸሎት ካሳለፈ በኋላ ኢየሱስ ዐሥራ ኹለት ደቀ መዛሙርትን መረጠ። ኹለት ኹለት እያደረገ ላካቸው። በአጋንንት ኀይሎችና በደዌ ኹሉ ላይ ሥልጣን ሰጣቸው።
እነዚህ ወንድማማቾቹ ጴጥሮስና እንድርያስ ናቸው...
ወንድማማቾቹ ያዕቆብና ዮሐንስ ...
ፊልጶስና ናትናኤል...


ቶማስና ቀደም ሲል ለሮማውያን ግብር ይሰበስብ የነበረው ማቴዎስ።
ታዴዎስና ሌላው ያዕቆብ...
ተቃዋሚ ጦረኛው ስምዖንና የአስቆሮቱ ይሁዳ።
ኺዱ፤ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።
12ቱ ሐዋርያት በጣም ተገርመው ከተላኩበት ቦታ ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋራ ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ መኼድ ፈለገ፤ ሕዝቡ ግን ከርሱ ተለይተው መኼድ አልፈለጉም።
መከሩ ሰፊ ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው። መከሩን የሚሰበስቡ ሠራተኞች እንዲልክ ወደ መከሩ ጌታ ጸልዩ።


ኢየሱስ እንደ ገና እያስተማረና እየፈወሰ ነበር፤ ቀኑ እየመሸ ነበር...
ፊልጶስ፣ እነዚህ ሰዎች በሙሉ እንዴት ምግብ ማግኘት ይችላሉ? ለምን የሚበሉትን አትሰጣቸውም?
የስምንት ወር ደመወዝ እንኳ እነዚህን ሁሉ ማጥገብ አይችልም!
እዚህ ዐምስት እንጀራና ኹለት ዓሦች ያሉት ልጅ አለ፤ ያለን ይኸው ብቻ ነው።
ሕዝቡን ኀምሳ ኀምሳ እያደረጋችኹ አስቀምጧቸው።
ኢየሱስ እግዚአብሔርን አመሰገነ...
እንጀራውንና ዓሣውን ቈራረሰ።


ኢየሱስ ያበረከተውን ምግብ በሺሕ የሚቈጠሩ ሰዎች በሉ...
ይህ ሰውዬ ይመጣል የሚባለው መሲሕ መኾን አለበት።
ንጉሣችን ልናደርገው ይገባል!
ተመልከቱ! ትርፍራፊው 12 መሶብ ሙሉ ኾኗል!
ሕዝቡ ወደየቤታቸው መኼድ አለባቸው፤ እናንተም በጀልባ ኾናችሁ ወደ ማዶ ኺዱ። እኔ ግን እዚሁ ተራራው ላይ ቆይቼ አጸልያለሁ።


በኋላም...
እእእ! መንፈስ መኾን አለበት!
አትፍሩ እኔ ነኝ!
ጌታ ኾይ፣ አንተ ከኾንኽስ በውሃው ላይ እየተራመድኹ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ!
ጴጥሮስ ና
ጌታ ኾይ አድነኝ!
ጴጥሮስ ለምን ተጠራጠርኽ?


ኢየሱስን ንጉሥ ማድረግ የፈለጉ ሰዎች ነበሩ። በርሱ መሪነት አገራቸውን የያዙ ሮማውያን ለቅቀው እንደሚኼዱ ተስፋ አድርገዋል። የኢየሱስ ተቃዋሚዎችም እየበዙ ነበር። ዘወትር ርሱን ይነቅፉት ነበር። ሕዝቡን በርሱ ላይ ማነሣሣትና ርሱን ጨርሶ ማጥፋት ፈልገዋል።
መምህር ወደዚህ መቼ መጣኽ?
እኔን የፈለጋችሁኝ ስለ ሰጠኋችሁ ምግብ ነውን?
ለዘለቄታ ለሚኖርና የዘላለም ሕይወትን ለሚሰጥ ምግብ እንጂ፣ በስብሶ ለሚጣል ምግብ አትጨነቁ፣
እኔ የዘላለም ሕይወት የሚሰጥ እንጀራ ነኝ። ዓለም ሕይወት እንዲያገኝ የተሰጠው የእኔ ሥጋ ነው።
ይህ ሰው እንድንበላ የራሱን ሥጋ የሚሰጠን እንዴት ነው?
የማይረባ!
ኑ ከዚህ እንኺድ!
ሰውን ሁሉ እያሳሳተ ነው።
እናንተም መኼድ ትፈልጋላችኹ?
ጌታ ኾይ፣ ወደ ማን እንኼዳለን? አንተ'ኮ የዘላለም ሕይወት ቃል አለኽ!



ኢየሱስ ላይ ተቃውሞ እየበዛ ነው። ኢየሱስ ወንዶችና ሴቶች ከነበሩበት የተከታዮቹ ቡድን ጋራ የገሊላን አካባቢ ትቶ ወደ ሌሎች የእስራኤል አካባቢዎች ኼዶ መሥራት ጀመረ።
ገሊላ
ኢየሩሳሌም
እስራኤል
በኋላም ወደ ኢየሩሳሌም አቀና።
እየኼደም እያለ...
ሰዎች ስለ እኔ ምን ይላሉ?
አንተ ነቢይ ነኽ ይላሉ።
እናንተስ?
እኔ ማን እንደ ኾንሁ ታስባላችኹ?
አንተ አዳኙ ነኽ፤ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነኽ።
ይህን ለማንም አትናገሩ፤ በዚያ መከራ ለመቀበልና ለመሞት መሲሑ ወደ ኢየሩሳሌም መኼድ ይኖርበታል። በሦስተኛው ቀን ግን ከሞት ይነሣል።


ብዙ ጊዜ ሰዎች የሚገደሉት ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጪ ነበር፤ የሚገደሉትም በአሰቃቂ ኹኔታ ተሰቅለው ሲኾን፣ ይህ ሮማውያን ወንጀለኞችን የሚቀጡበት መንገድ ነበር።
የእኔ መኾን የሚፈልግ ኹሉ ራሱን ከሌሎች መለየት አለበት፤ መስቀሉን ተሸክሞ እኔን መከተል አለበት።
ሕይወቱን አጥብቆ የሚይዝ ያጣዋል፤ ለእኔ ሲል ሕይወቱን የሚያጣ ግን መልሶ ያገኘዋል።
ይህን ማወቅ አለብህ፤ አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ።
በጣም አስፈላጊው ነገር በኹለንተናኽ እግዚአብሔርን መውደድ ነው፤ ራስህን እንደምትወድ ሌሎችንም መውደድ አለብህ!


በዚያ ዘመን በእስራኤል ለምጻሞች የሚኖሩበት ሰፈር ነበር። ለምጽ በጣም የሚያስፈራ የቆዳ በሽታ ነው። ይህ በሽታ ያለባቸው ከጤነኞች ጋራ እንዲነካኩ አይፈቀድም ነበር።
ለምጻም ሰዎች ከእነርሱ ጋራ እንዳይነካኩ ለማስጠንቀቅ፣ በሚኼዱበት ቦታ ኹሉ እየጮኹ ለምጻምነታቸውን መናገር ነበረባቸው።
ለምጻም! ለምጻም!
ጌታ ኢየሱስ ኾይ፣ እባክኽ ራራልን!



ኺደኽ ራስኽን ለካህን አሳይ!
ምርመራ እንዲደረግልኽ ወደ ካህን ኺድ
ፈውስ የምናገኘው ያኔ ነውን?
?
!
ተመልከቱ! ተፈውሻለኹ!
ተፈውሰናል!
አዎን!
ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር መልካም ነው! ተመስገን!
የተፈወሳችሁት 10 አልነበራችሁም? ታዲያ ሌሎቹ የታሉ? እግዚአብሔርን ለማመስገን አልመጡም ማለት ነው?
አንተ በሰላም ሂድ! እምነትኽ እንድትፈወስ ብቻ ሳይኾን እንድትድንም አድርጎኻል።


ኢየሱስ እየተጓዘ እያለ በኢየሩሳሌም የነበሩ የአይሁድ መሪዎች ርሱን እንዲሰልሉት ሰዎች ወደ ርሱ ላኩ። የሚያደርገውን ኹሉ ይቃወሙ ነበር።
ከአመንዝራዎችና ከሮማውያን ጋራ የሚሠሩ ግብር ሰብሳቢዎችን ከመሳሰሉ ሰዎች ጋራ ይቀራረባል...
መሲሑ የመጣው የጠፉትን ለመፈለግ ለማዳን ነው።
ኢየሱስ ማንም እንዲሠራ ባልተፈቀደበት በሰንበት ቀን በሽተኛ ፈወሰ...
ተፈወስ!
ሕፃናትም የተለየ ትኩረት አግኝተዋል...
ሕፃናት ወደ እኔ እንዳይመጡ አትከልክሉ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እነርሱን ለመሳሰሉ ሰዎች ናት።


ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ጥቂት ርቃ ወደ ነበረች ቢታንያ ወደምትባል ከተማ ተጠራ፤ አልዓዛር ታምሞ ነበር። አልዓዛር፣ ማርያምና ማርታ የሚባሉ ኹለት እኅቶች የኢየሱስ ወዳጆች ነበሩ። ኢየሱስ ቢታንያ ሲደርስ አልዓዛር ከአራት ቀን በፊት መሞቱን ሰማ።
ጌታ ኾይ፣
ጌታ ኾይ፣ አንተ እዚህ ኖረኽ ቢኾን ኖሮ ወንድሜ አይሞትም ነበር!
ማርታ ወንድምሽ ከሞት ይነሣል።
አዎን፣ በመጨረሻው ቀን ትንሣኤ ከሞት እንደሚነሣ ዐውቃለኹ።
ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን በሕይወት ይኖራል። ማርታ ይህን ታምኛለሽ?
አዎን ጌታ ኾይ! አንተ ወደ ዓለም እንደሚመጣ የተነገረለት አዳኙ የእግዚአብሔር ልጅ ነኽ።
የት ነው የቀበራችሁት?
ጌታ ኾይ፣ መጥተህ እይ!



ምን ያህል ይወደው እንደ ነበር ተመልከቱ።
አልዓዛር እንዳይሞት ማድረግ ይችል አልነበረምን?
የሞተው ሰው በጨርቅ ተጠቅልሎ ከዐለት በተሠራ መቃብር ውስጥ ተቀምጦ ነበር።
ድንጋዩን አንሡት!
ጌታ ሆይ፣ ከተቀበረ አራት ቀናት ስለኾኑት ይሸትታል...
የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ
አባት ሆይ፣ ይህን የምለው እዚህ የቆሙት አንተ እንደ ላክኸኝ እንዲያምኑ ነው።
አልዓዛር ሆይ፣ ና ውጣ!
የተጠቀለለበትን ጨርቅ ፍቱለትና ይኺድ።













ከዚያን ጊዜ ወዲህ የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ለሮማውያን አሳልፈው የሚሰጡበትን ምቹ ጊዜ ይጠብቁ ጀመር። የሞት ቅጣት የመፍረድ ሥልጣን ያላቸው እነርሱ ብቻ ናቸው።


ኢየሱስ በቢታንያ እያለ...
ማርያም!
ያ ሽቶ ከፍ ያለ ዋጋ የሚያወጣ ነው!
ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ይሻለን ነበር!
ይሁዳ፤ ርሷን ተዋት፤ ሥጋዬን ለመቃብር እያዘጋጀችው ነው።


በቅርቡ የፋሲካ በዓል ይከበራል፤ በጣም ብዙ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መምጣታቸው አይቀርም።


በኢየሩሳሌም መሪዎቹ ኢየሱስን ለመያዝ እያሤሩ ነበር፤ ያም ሆኖ ርሱ ወደ ከተማ ለመኼድ ጉዞ ጀምሯል።


ሕዝቡም በደስታና በሆታ ተቀበለውታል።
እንኳን ደኅና መጣኽ!
እንኳን ደኅና መጣኽ!
በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው!
አንተ የእስራኤል ንጉሥ!
ኢየሩሳሌም! ሰላምን እንዴት እንደምታገኚ ብታውቂ ኖሮ! ነገር ግን አትፈልጊም!
ዓለም ሁሉ እየተከተለው ነው’ኮ
በዚህ ሁኔታ የትም መድረስ አንችልም።


በዋናው ከተማ ያለው ቤተ መቅደስ፤ የአምልኮ ማእከል ነበር።
የፋሲካ በዓል በሚከበርበት ጊዜ፣ ብዙ በጐች ይታረዳሉ።
ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋራ ለማስታረቅ፣ በጐች ቤተ መቅደሱ ውስጥ መሥዋዕት ኾነው ይቀርባሉ
ግን፣ ሕዝቡን ከኀጢአት ነጻ የሚያደርገው የትኛው የመሥዋዕት በግ ይኾን?
ቤተ መቅደሱ አደባባይ ላይ ሰዎች የመነገድና ገንዘብ የመመንዘር ሥራ በዝቶባቸው ነበር።
ኢየሱስም እዚያ ነበር ...


የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት!
አደገኛ ሰው ነው፤ ሰዎች ርሱ የሚለውን ኹሉ ይቀበላሉ።
በተቻለ መጠን ቶሎ ርሱን ማጥፋት አለብን!


በዘዴ ብናጠምደው እጃችን ላይ ይወድቃል፤ ያኔ እኛ በቀላሉ እናስገድለዋለን።
ግን ይህ በበዓሉ ቀን መኾን የለበትም፤ በፋሲካ በዓል ምንም ሁከት እንዲፈጠር አንፈልግም።
ርሱን ይገኜ ባመጣላችሁ ስንት ትከፍሉኛላችኹ?
ይህ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አንዱ የኾነው ይሁዳ ነው!
እንግዲያስ ኢየሱስን አምጥቼ እሰጣችኋለኹ!
ኢየሱስን ይዘህ ብታመጣልን፣ የአንድ ባርያ ዋጋ ማለትም 30 ጥሬ ብር እንሰጥኻለን።



ምንም እንኳ መሪዎቹ ያንን ማድረግ አዳጋች ቢያደርጉበትም፣ ኢየሱስ ከፋሲካ በዓል በፊት የነበሩትን ቀኖች በቤተ መቅደስ ለሕዝቡ በመናገር እያሳለፈ ነበር።
በዚያ ምሽት ኢየሱስና 12ቱ ሐዋርያት የፋሲካን ምግብ ለመብላት በከተማው ተገናኝተው ነበር።
በዚህ ሌሊት ዛሬውኑ አደርገዋለኹ!


መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን የፋሲካ ምግብ ከእናንተ ጋራ ለመብላት እፈልግ ነበር።
ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሌሎች እንዲያገለግሏቸው ያደርጋሉ፤ በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ መኾን የለበትም።
ከእናንተ መካከል የኹሉም አገልጋይ የሆነው ርሱ መሪያችኹ ይኹን።
እኔ በመካከላችኹ ያለሁት እንደ አገልጋይ ነው።


ጌታ ኾይ፣ እንደ አገልጋይ እግሬን ልታጥብ ነው? በፍጹም እንደዚያ መኾን የለበትም!
ጴጥሮስ፣ እኔ ካላጠብኹኽ የእኔ መኾን አትችልም።
እንግዲያውስ ጌታ ሆይ፣ እግሬን ብቻ ሳይኾን እጄንና ራሴንም እጠበኝ!
ገላውን የታጠበ ሰው መታጠብ ያለበት እግሩን ብቻ ነው።
እናንተ ጌታና መምህር ትሉኛላችሁ፤ ያ ትክክል ነው። እኔ እግራችሁን እንዳጠብኹ እናንተም አንዳችኹ ሌላውን አገልግሉ።
ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል።
በፍጹም ሊኾን አይችልም!
መቼም እኔ አልኾንም፤ ነኝ እንዴ?
ይሁዳ ኾይ፣ የምታደርገውን ቶሎ ብለኽ አድርግ!


ይህን ዘወትር ለመታሰቢያዬ አድርጉት...
ይህን እንጀራ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው።
ይህን ጽዋ ጠጡ፤ ይህ ለእናንተ የሚፈስሰው ደሜ ነው። በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋራ ዐዲስ ኪዳን ያደርጋል።
ዐዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ ርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።
ይህ ፍቅር በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣ ኹሉም ሰው የእኔ ደቀ መዛሙርት መኾናችሁን ያውቃሉ።
ጌታ ኾይ፣ የትም ቢኾን እከተልኻለኹ፤ ለአንተ ስል ሕይወቴን እንኳ እሰጣለኹ።
ጴጥሮስ፣ ዶሮ ከመጮኹ በፊት አንተ ሦስት ጊዜ ትክደኛለኽ።



በኋላም በዚያው ምሽት ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከከተማ ወጡ፤ ይሁዳ ግን ከእነርሱ ጋራ አልነበረም...
ከእናንተ ተለይቼ እኼዳለኹ፤ አብ ግን መንፈስ ቅዱስን ይልክላችኋል፤ ርሱ ይረዳችኋል፤ ኹልጊዜም ከእናንተ ጋራ ይኾናል።
እኔ የምኼድበትን ቦታ መንገዱን ታውቃላችኹ።
እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ። በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አብ መምጣት አይችልም።
እዚህ ቆዩ፤ እኔ ለመጸለይ ጥቂት ራቅ ብዬ እኼዳለሁ።
አባት ኾይ፤ የሚቻል ከኾነ ይህን መከራ ከእኔ ውሰደው።
ነገር ግን፣ የእኔ ሳይኾን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም!


በእንዲህ ዐይነቱ ጊዜ እንዴት ትተኛላችኹ? ተነሡ! አሳልፎ የሚሰጠኝ መጥቷል!
እኔ የምስመውን ያዙት!
እንዴት ነህ መምህር!
ይሁዳ ኾይ፣ በመሳም መሲሑን አሳልፈህ ትሰጣለህን?
ጌታ ኾይ፣ ልዋጋቸው?
እረፍ!
ኢየሱስ እንዲይዙት ፈቀደ፤ ተከታዮቹም በየአቅጣጫው ሮጡ።


ኢየሱስ የአይሁድ መሪዎች ሁሉ የበላይ ወደ ነበረው ሊቀ ካህናት ተወሰደ። ጴጥሮስና ዮሐንስ በሩቅ እየተከተሉት ነበር።
ጴጥሮስ ወደ ግቢው ገባ።
አንተ ከእነርሱ ጋራ አልነበርኽም?
በፍጹም፣ ሌላው ቀርቶ ሰውየውን እንኳ አላውቀውም።
አንተም ከእነርሱ አንዱ ነኽ አይደል?
በፍጹም አይደለሁም!
እዚያ እንደ ነበርኽ ርግጠኛ ነኝ! አንተ የገሊላ ሰው አይደለህም?
ምን እያልሽ እንደ ኾነ አይገባኝም።


ኩኩሉ
ከዚያም
እስቲ ትንቢት ተናገርልን፤ ለመኸኑ የመታህ ማን ነው?
ጧት ላይ ኢየሱስን ወደ አይሁድ መሪዎች ጉባኤ አቀረቡት።
አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነኽ?
አንተ አልኸ።
ስድብ ነው! መሞት ይገባዋል፤ ሮማውያን ይፍረዱበት!


ኢየሱስ ጲላጦስ ወደሚባል ሮማዊ ባለሥልጣን ተወሰደ፤ የአይሁድ መሪዎች ሕዝቡን ቀሰቀሱ፤ ማንኛውንም ዐይነት ክስ መሰንዘር ጀመሩ።
ለሚሰነዘርብህ ክስ ኹሉ ምን ትላለህ? ዝም ማለት ብቻ?
ለመሆኑ፣ ያደረግኸው ምንድነው?
ለእውነት ለመመስከር መጥቻለሁ።
እውነት ምንድነው?
ምንም በደል አላገኘሁበትም፤ እንደምታውቁት የፋሲካ በዓል ሊመጣ ነው። ታዲያ፣ ማንን ልፍታላችሁ፣ በርባንን ወይስ የአይሁድ ንጉሥን?


በርባንን!
በርባንን!
ይህ ኢየሱስ የሚባለውንስ ምን ላድርገው?
ስቀለው!
ንጉሥ እንደ ኾነ ያስባል!
ርሱን ከፈታኸው እንግዲያው የቄሳር ወዳጅ አይደለኽም።
በርሱ ፈንታ ነጻ ኾነሃል።
በርባን ተፈታ፤ ርሱ በፖለቲካዊ ግድያ ተፈርዶበት ነበር።
...37፣ 38፣ 39!
እኔ ከደሙ ንጹሕ ነኝ።
ሰላም ለአንተ ይኹን የአይሁድ ንጉሥ!


ሰውየውን እዩት!
ስቀለው!
ስቀለው!
ስቀለው!
ጲላጦስ ፍርዱን አጸደቀ። ተሰቅሎ መሞት እጅግ ዘግናኝ ሞት ነበር። ኢየሱስ ይህን የሚሰቀልበትን የመስቀሉን ግንድ ተሸክሞ በኢየሩሳሌም መንገዶች ኼደ።
የመገደያው ቦታ ከከተማው ውጪ ነበር፤ ጐልጐታ፣ ወይም የራስ ቅል ቦታ ይባል ነበር።
እዚያ ወታደሮቹ ኢየሱስን መስቀል ላይ ቸነከሩት።


በዚሁ ጊዜ ይሁዳ ካደረገው ክፉ ነገር የተነሣ በጣም እየተጸጸተ ነበር።
በጣም ተሳስቻለኹ።
ንጹሕ ሰው አሳልፌ ሰጥቻለኹ።
ያ ከእኛ ጋር ምን ያገናኘዋል፧ የራስህ ጉዳይ ነው!
ኢየሱስ በኹለት ወንጀለኞች መካከል ተሰቀለ።
አባት ኾይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።


መስቀሉ ላይ "ኢየሱስ፣ የአይሁድ ንጉሥ" የሚል ጽሑፍ በሦስት ቋንቋዎች ተጻፈ።
IESVS NAZARENVS REX IVDAEORVM
ΙΗΣΟΥΣ Ο ΝΑΖΩΡΑΙΟΣ
Ο ΒΑΣΙΛΕΥΣ ΤΩΝ ΙΟΥΔΑΙΩΝ
ኢየሱስ የሥቃይ ማስታገሻውን መጠጣት አልፈለገም።
ወታደሮቹ ልብሶቹ ላይ ዕጣ ይጣጣሉ ነበር።
አዎን፣ ሌሎችን አድኖ አልነበር?
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፣ እስቲ ከመስቀሉ ውረድ!
ራስህንና እኛንም አድን!
እግዚአብሔርን ፍራ፤ እኛ የሚገባንን አግኝተናል፤ ይህ ሰው ግን ምንም በደል አላደረገም።
ወደ መንግሥትህ ስትገባ አስበኝ!
በዛሬው ቀን ከእኔ ጋራ በገነት ትሆናለህ።


6 ሰዓት ሲኾን ፀሓይ ጨለመች፤ ጨለማ ኾነ።
የኢየሱስ እናት ማርያምና ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ መስቀሉ አጠገብ ቆመው ነበር።
ከእንግዲህ እናትና ልጅ ናችኹ።
አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
ተጠማኹ!
አባት ኾይ፣ መንፈሴን በእጅኽ አደርጋለሁ።
ተፈጸመ!


ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ኢየሱስ ሞተ፤ አንዱ ወታደር የኢየሱስን ጐን በጦር ሲወጋው ውሃና ደም ወጣ።
በመጽሐፍ፣ "እንደ በግ ወደ ሞት ተነዳ" ይላል።
"ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችን ደቀቀ።" አኹን ግን ሞቷል።
ርሱ ይመጣል የተባለው መሲሕ ይኾን እንዴ?
እስቲ እንድንቀብረው ይፈቀድልን ከኾነ እንጠይቅ።
የአርማትያሱ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የኢየሱስን አስከሬን ወሰዱ፤ ጣፋጭ ቅመም በተነሰነሰበት የበፍታ ጨርቅ ጠቅልለው በትልቅ ድንጋይ በተዘጋ መቃብር ውስጥ አኖሩት።


ከሰንበት በኋላ ጥቂት ሴቶች በድንጋይ ወደ ተገጠመው መቃብር ኼዱ...
ድንጋዩ ተንከባልሎ ነበር!
ሕያው የኾነውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጉታላችሁ? ርሱ ተነሥቷል፤ ኼዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ተናገሩ!
ይህን ሲሰሙ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ወደ መቃብሩ ኼዱ።
ምንድነው የኾነው?
መቃብሩ ባዶ ነው!



መቃብሩ አጠገብ በነበረው አትክልት ቦታ...
አንቺ ሴት ለምን ታለቅሻለሽ? ማንን እየፈለግሽ ነው?
ጌታው፣ አንተ ወስደኸው ይኾን?
ማርያም!
መምህር!
አትንኪኝ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እንደምኼድ ለወንድሞቼ ንገሪያቸው።


በዚያው ቀን ተስፋ የቈረጡ ኹለት የኢየሱስ ተከታዮች ስለ ኢየሱስ መገደል ከአንድ መንገደኛ ጋራ እየተነጋገሩ ነበር...
ነቢያትን አታምኑም ማለት ነው? ወደ ክብሩ እንዲገባ መሲሕ መከራ መቀበል የለበትምን? ይህ ኹሉ'ኮ በመጽሐፍ ተጽፏል!
ምግብ እየበሉ እያለ እንግዳው ሰውዬ በድንገት ተሰወረ...
ያ ሰው ኢየሱስ ራሱ ነበር!
እነርሱም ወዲያውኑ ሌሎች የኢየሱስ ተከታዮችን ለማግኘት ኼዱ።
ጌታን አይተነዋል!
ማርያምና ጴጥሮስም አይተውታል!
በድንገት...
ሰላም ለእናንተ ይኹን!
እኔ መኾኔን አታምኑም? እጆቼንና እግሮቼን ተመልከቱ!
ጌታዬና አምላኬ!


በሚቀጥሉት 40 ቀናት ውስጥ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ተገለጠላቸው፤ በአንድ ጊዜ ከ500 በላይ የሚኾኑ ሰዎች አይተውታል። አንድ ቀን ከሐዋርያት አንዳንዶቹ በገሊላ ባሕር ዓሣ እያጠመዱ ነበር።
የሚበላ ነገር አላችሁ?
የለም፤ ምንም አልያዝንም!
መረብኽን ወደ ባሕሩ ጣል!
በጣም ይገርማል! ብዙ ዓሦች ያዝኹ!
ጌታ'ኮ ነው!
መምህር!
መጥታችሁ ከእኔ ጋራ አትበሉም?


ጴጥሮስ፥ በርግጥ ትወድደኛለኽ?
ኢየሱስ ይህን ጥያቄ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ ጠየቀው…
አዎን ጌታ ኾይ፣ እንደምወድድኽ ታውቃለኽ?
እንግዲያው በጐቼን አሰማራ!
ተከተለኝ!
በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ተሰጥቶኛል፤ ወደ ዓለም ኼዳችሁ ሕዝቦችን ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፣ የነገርኋችሁን ሁሉ እንዲያደርጉ አስተምሯቸው።
እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በእያንዳንዱ ቀን ከእናንተ ጋራ መኾኔን አትርሱ።
ይህን ከተናገረ በኋላ ኢየሱስ ምድርን ትቶ ወደ ሰማይ ኼደ። ይሁን እንጂ፣ በሕዝቦች ኹሉ ላይ ለመፍረድ እንደሚመጣም ተናግሮአል።

ተከታዮቹ በጸሎት እየተጠባበቁ በኢየሩሳሌም ነበሩ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። ኢየሱስ ውስጥ የነበረው ያው መንፈስ አሁን በእነርሱም ውስጥ ይኖራል። በኀይልና በሥልጣን ስለ ኢየሱስ የሚመሰክሩ ዕዱስ ሰዎች ያደርጋቸዋል።










አሁን በመላው ዓለም ያሉ የኢየሱስ ተከታዮች ለመጸለይና መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ይሰበሰባሉ፤ የኢየሱስን ሞት እንዲያሳስባቸው እንጀራውን ይቈርሳሉ ወይኑን ይጠጣሉ። ልባቸው ውስጥ ያለውን የርሱን ፍቅር በዙሪያቸው ላሉት ሰዎች እንዲያካፍሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።


ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለው ዓላማ እውን እንዲኾን አድርጓል።
ኢየሱስ ይወድደናል! ርሱን ማመስገንና ማምለክ አለብን!
እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን ወድዷል፤ በርሱ የሚያምን ኹሉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል እንጂ ከእንግዲህ አይጠፋም።
WILLEM DE VINK

## መጽሐፍ ቅዱስ

የኢየሱስ ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል። ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ ብዙ ጊዜ የተነበበና በመነበብ ላይ ያለ አንድም መጽሐፍ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጽሐፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው። እነዚህን መጽሐፎች ለመጻፍ 1500 ዓመታት ወስዷል። መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ የተጠናቀቀው ከ1900 ዓመታት በፊት ነበር። እግዚአብሔር በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ያደረገውን ተሳትፎ በተመለከተ አያሌ ታሪኮችን አካትቶአል። የኢየሱስ ታሪክ ከምንም የበለጠ የእግዚአብሔርን ማንነት በግልጽ ያሳያል።

## የኢየሱስ ታሪክ



መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ታሪክ የሚናገሩ 4 መጽሐፎችን ይዞአል። መጽሐፎቹ የሚጠሩት በጸሐፊዎቻቸው ስም ነው፡ ጸሐፊዎቹ ሁሉ ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ዘመን የኖሩ ናቸው።

1. **ማቴዎስ** - የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነው። ሥራው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር። ኢየሱስ የእስራኤልን ሕዝብ (አይሁድ) በተመለከተ ያደረገውንና የሆነውን ይገልጣል።

2. **ማርቆስ** - ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን ገና በዐሥራዎቹ ዕድሜ የነበረ ወጣት ነበር፤ ኢየሱስ ከፈጸማቸው ተአምራት በጣም ጥቂቶቹን በጽሑፍ አኑሮልናል።

3. **ሉቃስ** - የሕክምና ዶክተር ነበር፤ በግል ኢየሱስን አላገኘውም፤ ሰዎችን በተመለከተ ኢየሱስ ያደረገውንና የሆነውን ሉቃስ ይገልጣል።

4. **ዮሐንስ** - እርሱም የኢየሱስ ተከታይ ነበር፤ በዋነኛነት ደረጃ የኢየሱስን ማንነት ያሳያል። ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ነጻ ለማድረግ ሰው የሆነ እግዚአብሔር ነው።

## የኢየሱስ መወለድ

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ እናቱ ማርያም ባል ያላገባች፤ ድንግል ነበረች። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ኢየሱስ እንዲወለድ አደረገ። ይህ ተአምር ኢየሱስ ከመወለዱ ረጅም ዓመታት በፊት በመጻሕፍት ተጽፎ ነበር። ኢየሱስ እንደ አንድ ጀግና ወይም ታዋቂ ሰው አልነበረም የተወለደው። ሌላ ምንም ክፍል ስላልነበር እርሱ በረት ውስጥ ነበር የተወለደው።

## የኢየሱስ ተአምራት

ኢየሱስ ብዙ ተአምራት አድርጓል። መጽሐፍ ቅዱስ ከ40 የበለጡ የፈውስ ታሪኮች ይዞአል። በእነዚህ ተአምራት በኩል ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ኃይልና ፍቅር፣ እንዲሁም እርሱ ሰዎችን ለመርዳትና ደስተኞች እንዲሆኑ እንደሚፈልግ አሳየ።





# የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ



***ኢየሱስ የሞተው ለምን ነበር?መልሱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል።***

ሰዎች ሁሉ አንዳንድ መጥፎ ነገሮች ያደርጋሉ። እነዚህን ነገሮች እግዚአብሔር አይፈልጋቸውም፤ እንዲያውም በጣም ያስቆጡታል ወይም ያሳዝኑታል። እንዲህ ያሉ ነገሮች ኃጢአት ይባላሉ። እነዚህ ኃጢአቶች ሰዎች የእግዚአብሔር ወዳጆች እንዳይሆኑ ያደርጋሉ።
ኢየሱስ የመጣው በዚህ ምክንያት ነበር። በገዛ ራሱ ፈቃድ ኢየሱስ የኃጢአታችንን ቅጣት ወሰደ። ያ ቅጣት ሞት ነበር። ኢየሱስ ለእኛ በመሞቱ እንደ ገና የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆን እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ በኃጢአታችን ማዘንና መጸጸት አለብን።
ኢየሱስ ከሞት ተነሣ። እግዚአብሔር እንደ ገና ወደ ሕይወት አመጣው። ይህን በማድረጉ እግዚአብሔር ከሞት የበለጠ ብርቱ መሆኑን አሳየ።
አሁን ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እየኖረ ነው። እርሱ ሕያው ስለሆነ ሁልጊዜ ወዳጃችን መሆን ይችላል። እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ መኖር እንድንችል ሊረዳን ይፈልጋል።

## ጸሎት

*በኃጢአትህ አዝነህና ተጸጽተህ ከሆነና የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን ከፈለገህ ይህን የመሰለ ጸሎት ጸልይ፣*
*“እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ ትወደኛለህ።*
*አንድ ልጅህ ኢየሱስን ሰጥተሃል።*
*እኔ ለፈጸምኋቸው ኃጢአቶች በሙሉ እርሱ መስቀል ላይ ሞተ።*
*እባክህን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፤ በኃጢአቴ አዝኛለሁ።*
*ኢየሱስ የእኔ ወዳጅ ስለሆነ ተመስገን።*
*ምንጊዜም የአንተ መሆን እፈልጋለሁ።*
*መኖር እንደምትፈልገው መኖር እንድችል እርዳኝ።*
*ሁሌም ከእኔ ጋር ሁን።*
*ጸሎቴን ስለ ሰማህ ተመስገን።*
*አንተ ቃልህን እንደምትፈጽም ዐውቃለሁ!”*

# ኢየሱስና አንተ

የኢየሱስ ታሪክ መልካም ፍጻሜ አለው። ያኔም ሆነ አሁን በዚህ ዘመን ኢየሱስ የብዙ ሰዎች ወዳጅ ነው። ዓለም ተለውጧል፤ በዚህ ዘመን ሰዎች በመኪናና በአውሮፕላን እንጂ በአህዮች ወይም በፈረሶች አይጓጓዙም። ለኢየሱስ ግን ይህ ልዩነት ምንም ማለት አይደለም። በጥንት ዘመን በእስራኤል እንደ ነበረው ሁሉ ዛሬም እርሱ አጠገባችን ነው።
በዓይን ላይታይ ይችላል፤ ይሁን እንጂ፣ እውን ነው። ዛሬ ወዳጅህ መሆን ይፈልጋል። ልትሰማውና ልትወደው ይገባል።

ስለ ኢየሱስና ከእርሱ ጋር መኖር ስለሚቻለው ሕይወት የበለጠ ማወቅ ትፈልጋለህ? እንደዚያ ከሆነ የሚከተሉትን አድርግ

1. **በግልህ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ጀመር፤** ለምሳሌ ከሉቃስ ወንጌል መጀመር ትችላለህ።

2. **መጸለይ ጀምር**
(ከእግዚአብሔር ጋር ስንነጋገር - ልዩ የሆነ ቃላት መጠቀም አያስፈልግም)

3. **ስለ ኢየሱስና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ለሌሎች ሰዎች ተናገር።**የበለጠ መማር እንዲችሉ ተከታዮቹ በአንድነት እንዲገናኙና እርስ በርስ እንዲበረታቱ ኢየሱስ ይፈልጋል።



*ጽሑፍ እና ሥዕል፦ ዊልያም ዴ ቪንክ*
*የቅጅ መብት © እ.ኤ.አ.1993 ስቲችቲንግ ዌሬልድታል፣ ሕዩተን፣ ኔዘርላንድ በደች ቋንቋ “Jezus Messias”ተብሎ ታትሟል።*
*የአማርኛ እትም © እ.ኤ.አ.2018, 2024*
*የዲጂታል ቅጂ መብት በCreative Commons BY-SA ፈቃድ ተወስኗል።*
*የሁሉም አገራት የመተርጎም፣ የማባዛት እና የመመለስ መብት የተጠበቀ ነው።*
*ኢሜል: jmpbk.app@gmail.com*
*https://jesusmessiahcomicmedia.com/ethiopia*

መሲሑ ኢየሱስ ይህ የኢየሱስ መሲሕ እውነተኛ ታሪክ ነው። እርሱ ከ2000 ዓመታት በፊት በእስራኤል ይኖር ነበር። ከእርሱ ጋር የተገናኙ ሁሉ ይደነቁ ነበር። እርሱ ያደረገውን ማንም አላደረገም። እርሱ የተናገረውን ማንም አልተናገረም። ኢየሱስ በነበረበት ስፍራ ሁሉ ተአምራት ይደረጉ ነበር። እርሱን ለሰሙት ሁሉ ደስታንና ሐሤትን አምጥቶላቸዋል። ግን በድንገት ሁሉም አበቃ። ተቀዋሚዎቹ ገደሉት። ያ ግን የመጨረሻው አልሆነም። ምን እንደ ሆነና የኢየሱስ መሲሕ ታሪክ እንዴት እንደ ቀጠለ አንተ ለራስህ አንብብ!




ቋንቋ: አማርኛ (ኢትዮጵያ)
language: Amharic (Ethiopia)
ISBN: 978-90-73150-62-1